6ኛ ዓመት ቁጥር 6
6th Year No. 6

ሐረር ሐምሌ 18 ቀን ፲1993
HARAR JULY 25/ 2001

የሐረሪ ሕዝብ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት

# ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ

# HARAR NEGARI GAZETA

HARARI PEOPLE NATIONAL REGIONAL STATE

| የአንዱ ዋጋ ብር 0.50 | በሐረሪ ሕዝብ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ተጠባባቂነት የወጣ | የፖስታ ሣጥን ቁጥር 272 |
|---|---|---|

ማዉጫ

አዋጅ ቁጥር 27/1993
የሐረሪ ሕዝብ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት የሚሊሺያ ጽ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 27/1993. . . . . . . . . . . . . . ገጽ244

## አዋጅ ቁጥር 27/1993 ዓ.ም
## የሐረሪ ሕዝብ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የሚሊሺያ ጽ/ቤት ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

በክልሉ ዉስጥ ፍትህን በማስከበርና ሠላምና ጸጥታን በማረጋገጥ ረገድ ከመስተዳድሩ የፍትህ አካላት ጋር ተጋግዞ የሚሰራ እና ህዝቡ ያገኛቸዉን መብቶችና ጥቅሞች በአመፅ ለመንጠቅ የሚደረገዉን ማንኛዉንም እንቅስቃሴ የሚከላከል የሚሊሺያ ኃይል በህዝብ ተሳትፎ ማደራጀት በማስፈለጉ፣ የሚደራጃዉ የሚሊሺያ ኃይል የሚተዳደርበትን ሁኔታ በዝርዝር መወሰንና የሚሊሺያ ኃይሉን የሚያደራጅ የሚያስተባብርና የሚቆጣጠር አካል ማቋቋም በማስፈለጉ፡

በሐረሪ ሕዝብ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ህገ መንግስት አንቀፅ 26 ንዑስ አንቀፅ 2/ሀ/ መሠረት ከዚህ የሚከተለዉ ታዉጇል፡፡

## ምዕራፍ አንድ
## ጠቅላላ

### 1 አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ የሐረሪ ሕዝብ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የሚሊሺያ ጽ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 27/1993 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2 ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ዉስጥ የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠዉ ካልሆነ በስተቀር :-

1. "ሚሊሺያ" ማለት፡- በልዩ ሁኔታ አስገዳጅነት ካልሆነ በስተቀር ከምርት ተግባሩ ወይም ከመደበኛ ሥራዉ ሳይነጠል በመስተዳድሩ ወይም በግሉ በታጠቀዉ የጦር መሳሪያ ፀጥታ ለማስከበር በቀበሌዉ ነዋሪ ህዝብ የተመረጠና የደመወዝ ክፍያ የማይከፈለዉ ሰዉ ነዉ::
2. "ክልል" ማለት በሐረሪ ሕዝብ ብሄራዊ ክልል ሕገ መንግስት አንቀፅ 2 መሰረት የተቋቋመዉ የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልል ነዉ::
3. "ምክር ቤት" ማለት፡- የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ነዉ::
4. "ኮሚቴ" ማለት፡- የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ነዉ::
5. "ኃላፊ" ማለት :- የክልሉ የሚሊሺያ ጽ/ቤት ዋና ኃላፊ ነዉ::
6. "ደንብ" ማለት፡- እንደ አስፈላጊነቱ ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም የክልሉ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚወጣዉ ደንብ ነዉ::
7. "ሰዉ" ማለት፡- የተፈጥሮ ሰዉ ወይንም ህጋዊ ሰዉነት መብት የተሰጠዉ አካል ነዉ::
8. "ሐይል" ማለት፡- የታጠቀ የሚሊሺያ ሐይል ሲሆን ከሁለት በላይ ጋንታ ይኖረዋል ወይም ይይዛል::
9. "ጋንታ" ማለት፡- ከሀይል በታች ያለ አካል ሲሆን ከሀያ ያልበለጠ ሚሊሺያ የሚይዝ ነው::

## ምዕራፍ ሁለት
## የሚሊሺያ ጽ./ቤት
## መቋቋም ፣ ዓላማ ፣
## አደረጃጀትና ተጠሪነት

## ክፍል አንድ
## ስለ ሚሊሺያ ጽ/ቤት
## መቋቋምና ዓላማ

3 ስለ ጽ/ቤቱ መቋቋም

የሐረሪ ሕዝብ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የሚሊሺያ ጽ/ቤት ከዚህ በኃላ ጽ/ቤት እየተባለ የሚጠራ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል::

4 የጽ/ቤቱ ዓላማ

ጽ/ቤቱ የሚከተለዉ ዓላማ ይኖረዋል፡- የክልሉ ነዋሪ ህዝብ የሚሊሺያ ኃይል አደራጅቶ ሰላምና ፀጥታን በማስከበር ረገድ ተሳትፎ እንዲያደርግ የማስተባበርና የሚሊሺያ ኃይልን የመምራት ዓላማ ይኖረዋል::

## ክፍል ሁለት
## የሚሊሺያ ጽ/ቤት አደረጃጀትና
## ተጠሪነት

5 የጽ/ቤት አደረጃጀት

1. ጽ/ቤት
   ሀ/ የክልል ጽ/ቤት
   ለ/ በደንቡ መሰረት በየአስተዳደር እርከኑ የሚዋቀር ሐይልና ጋንታ ይኖረዋል ዝርዝሩ በደንቡ ይወሰናል::
   ሐ/ በየቀበሌዉ የሚደራጅና በሚመለከተዉ የቀበሌ አስተዳደር ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በሚሰየም ሰብሳቢ የሚመራ ከ3 ያላነሱ አባላት ያሉት የቀበሌ ሚሊሺያ ኃይል ኮሚቴ ይኖረዋል::
2. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ አንድ /ሀ/ የተመለከተዉ ጽ/ቤት ኃላፊ

ኮሚሰርና መረጃ ክፍል እንዲሁም ለሥራዉ አስፈላጊ የሆኑ ሰራተኞችና የሥራ ክፍሎች ይኖረዋል::

6 ተጠሪነት

1. ጽ/ቤቱ ተጠሪነቱ ለኮሚቴዉ ይሆናል::
2. እያንዳንዱ የቀበሌ ሚሊሺያ ኃይል ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለቀበሌዉ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይሆናል::

7 አሿሿም

ኃላፊው ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ተመርጦ በኮሚቴው አቅራቢነት በምክር ቤቱ ይሾማል::

## ምዕራፍ ሦስት
## የጽ/ቤት፣ የኃላፊና የሚሊሺያ ሥልጣንና ተግባር

### ክፍል አንድ
### የጽ/ቤቱ ሥልጣንና ተግባር

8 ሥልጣንና ተግባር

ጽ/ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

1. በየደረጃዉ የሚቋቋሙ ጽ/ቤቶችንና ኮሚቴዎችን ያደራጃል ያስተባብራል ፣ ይመራል፣
2. በዚህ አዋጅና ኮሚቴው በሚያወጣው ደንብ መሠረት ለሚቋቋመዉ ሚሊሺያ የሰዉ ኃይል ይመለምላል፣ ያሰለጥናል፣ ያደራጃል፣ ያስታጥቃል፣ ያስማራል ፣ ብቃታቸዉን ለማሳደግ በሚያስችል መልኩ ሥራን በበላይነት ይመራል፣
3. በህጉ መሰረት ወንጀል እንዳይፈፀም ይከታተላል ፣ ይከላከላል፣ ይቆጣጠራል ከህዝባዊ ፖሊስና ከህዝቡ ጋር በመተባበር የአካባቢ ፀጥታ ኃይል ሆኖ ይሰራል፣
4. ሚሊሺያዉ በልዩ ሁኔታ አስገዳጅነት ካልሆነ በስተቀር ከምርት ሥራዉ ወይም ከመደበኛ ሥራዉ በሚነጥል ተግባር እንዳይሰማራ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣
5. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለሀገር ሰላምና ደህንነት ከሀገር መከላከያ ሰራዊት ጋር ይሰራል፣
6. በሚወጣዉ ደንብ መሰረት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 ንኡስ ዓንቀፅ 1 ለ እና ሐ መሰረት የሚቋቋሙትን አካላት ያስተዳድራል፣
7. ዕቅድና በጀት አዘጋጅቶ ያቀርባል ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፣
8. እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች ተገቢነት ያላቸዉ ተግባራት ያከናዉናሉ::

### ክፍል ሁለት
### ኃላፊ ሥልጣንና ተግባር

9 ሥልጣንና ተግባር

ኃላፊ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 7 ላይ ለጽ/ቤቱ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት የሚያከናዉን ሲሆን በተጨማሪም የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል:-

1. ጽ/በቱን ይመራል፣ ይወክላል፣
2. የጽ/ቤቱን እቅድ እና በጀት ያዘጋጃል ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፣
3. የጽ/ቤቱን የሥራ እንቅስቃሴ በሚመለከት ለኮሚቴዉ በየሩብ ዓመቱ እንዲሁም ወቅቱን ጠብቆ ለምክር ቤቱ ሪፖርት ያቀርባል::

## ክፍል ሦስት
## የሚሊሺያ ሥልጣንና ተግባር እና የሚሊሺያ ምልመላ

### 10 የሚሊሺያ ሥልጣንና ተግባር

1. ወንጀል እንዳይፈፀም ይከታተላል፣ ይከላከላል፣ ከህብረተሰቡና ከህዝባዊ ፖሊስ ጋር በመተባበር የአካባቢዉ የፀጥታ ኃይል ሆኖ ይሰራል።
2. ወንጀል ሲፈፅም የተገኘዉን ሰዉ በህጉ መሰረት ይይዛል ወዲያዉኑ ከኤግዚቢቱና ዝርዝር ሪፖርት በአቅራቢያዉ ለሚገኝ ፖሊስ ያስረክባል።
3. በአካባቢዉ የአስተዳደርና ፍትህ አካላት የሚሰጡትን ተልዕኮዎችን ይፈፅማል
4. በሽፍተኝነትና በስርቆት የተሰማራ እንዲሁም የወንጀል ድርጊት ለመፈፀም የተደራጁና ህግ የሚጥሱ ሰዎች መኖራቸዉን ሲገነዘብ በፍጥነት ለሚመለከታቸዉ አካላት ያሳዉቃል የአካባቢዉን ህብረተሰብ በማስተባበር በቁጥጥር ስር የሚዉሉበትን እርምጃ ይወስዳል።
5. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለሃገር ሰላምና ደህንነት ከሃገር መከላከያ ሠራዊት ጋር ይሰራል።

### 11 የሚሊሺያ አባላትና ምልመላ

1. ማንኛዉም ዕድሜዉ ከአሥራ ሰምንት ዓመት እስከ 40 ዓመት የሆነ ጤናማ አእምሮና አካላዊ ብቃት ያለዉ የታዉ ወንድ የሙያ ልዩነት ሳይደረግ በክልሉ ዉስጥ በሚገኙ ቀበሌዎች ነዋሪ የሆነ ጥሩ ስነ-ምግባር ያለዉ ኢትዮጵያዊ በፍላጎት የሚሊሺያ አባል ሊሆን ይችላል።
2. የሚሊሺያ አባላት ምልመላ በአካባቢዉ ነዋሪዎች ቀጥታኛ ተሳትፎ የሚመረጥ ሲሆን የአፈፃጸሙ ዝርዝር ወደፊት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል።
3. ማንኛዉም የሚሊሺያ አባል የሆነ ከአባልነት የመሰናበት መብት አለዉ። ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።

## ምዕራፍ አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 12 ስለ ትጥቅ ህጋዊነት

1. በሚወጣዉ የሚሊሺያ ደንብ መሠረት ተመልምሎ የሚታጠቅ የሚሊሺያ ሠራዊት አባል ህጋዊ ታጣቂ መሆኑን የሚያረጋግጥ መታወቂያ ደብተር ይኖረዋል።
2. ማንኛዉም የሚሊሺያ አባል የሚይዘዉን ትጥቅ ህጋዊ በሆነ መንገድ ለተሰጠዉ ሥልጣንና ተግባር ብቻ ይገለገልበታል።
3. ማንኛዉም ሚሊሺያ በመንግስት የተሰጠዉን ትጥቅ መሸጥ፣ ሚሊሺያ ላልሆነዉ አሳልፎ መስጠት፣ መለወጥ፣ ማከራየት እና ማበላሸት በህግ ያስቀጣል።

### 13 ደንብ የማዉጣት ሥልጣን

ስለ ሚሊሺያ ምልመላና ሥልጠና ፣ ሥነ-ምግባርና ስንብት የሚመለከቱ ጉዳዮችና ሌሎች ጉዳዮችን በተመለከተ ኮሚቴዉ ደንብ ያወጣል።

### 14 በጀት

የጽ/ቤቱ በጀት በክልሉ መንግስት ይመደባል።

15 <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በሐረሪ ነጋሪ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ሐምሌ 18 ቀን 1993 ዓ.ም
ሐረር
ፉአድ ኢብራሂም
የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ
መንግስት
ፕሬዝዳንት